# “ግንቦት ሃያ” ወዴት አመራችን?

አባ መላኩ 05-08-18

“ግንቦት ሃያ” ወዴት አመራችን? የሚል ርዕስ ለዛሬ አተታዬ መነሻ እንዲሆነኝ የፈለኩት ኢትዮጵያ “በግንቦት ሃያ” ድል ከየት ተነስታ የት እንደደረሰች አንዳንድ ሃሳቦችን ለማንሳት ስለፈለኩ ነው። የመጀመሪያውና ትልቁ ቁምነገር ዛሬ እንዲያና እንዲህ የምንባባልባት አገርን ከመበታተን አደጋ የታደገችልን ዕለት “ግንቦት ሃያ” ናት። “ግንቦት ሃያ” የኢዮጵያን ብሄሮች ብሄረሰቦችና ህዝቦች ከአፈና ስርዓት አላቃቸው ነጻነታቸውንና እኩልነታቸውን አረጋግጣላቸዋለች። “ግንቦት ሃያ” አገራችንን ከከፋ ድህነት እንድትላቀቅ ምክንያት ሆናለች፤ የዜጎች ዓመታዊ የነፍስ ወከፍ ገቢ ከ800 ዶላር ዘሏል፤ በህይወት የመኖር ጣሪያውም ወደ 67 ዓመት ከፍ ብሏል።

ከግንቦት 20 ቀን 1983 ዓ.ም በፊት አገራችን አይኗን ታስራ በገደል አፋፍ ላይ እንደቆመች ሰው ተደርጋ የምትወሰድ ደረጃ ላይ ነበረች። በአገሪቱ የድህነት መጠኑ እጅግ የከፋበት፣ የአገሪቱ ኢኮኖሚ ያዘቀጠበት፣ ህዝቡ ተስፋ የቆረጠበትና አገሪቱ የመበታተን አደጋ ላይ ነበረች። ለ17 ዓመታት ለነጻነትና እኩልነት የተደረገው የእርስ በርስ ጦርነት ማብቃቱን ተከትሎ በርካታ በብሄር፣ በሃይማኖት፣ ወዘተ የታጠቁ ሃይሎች ፍላጎታቸውን በሃይል ለማሳካተ ሲሯሯጡ የነበሩበት ወቅት ነበር። ይሁንና በወቅቱ ትልቅ ሃላፊነት የተጣለበት ኢህአዴግ የሁሉንም ሃይሎች ፍላጎት ማሳካት የሚችል አካሄድ መከተል በመቻሉ አገራችንን ከውድቀት ታድጓታል።

ከግንቦት 20 ቀን 1983 ዓ.ም ወዲህ የመጣውን ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ለውጦች ለመረዳት ቀደም ሲል የነበረውን ሁኔታ በትክክል መገንዘብን ይጠይቃል፡፡ አንዳንዶች የባለፉት ስርዓቶች ማለትም የአጼዎቹና የደርግ መንግስት ሲነሱ አይወዱም። ይሁንና እውነታው ግን መታወቅ አለበት። መነሻውን የማያውቅ መድረሻውን አያውቅም እንደሚባለው ግንቦት 20 ከያት አንስታን የት እንዳደረሰችን ለማወቅ የቀድሞውን መነሻ ማስታወስ ተገቢ ነው። በእርግጥ ዛሬን ከአጼዎቹ ስርዓት ጋር ይወዳደር ማለቴ እንዳልሆነ ግን መታወቅ የኖርበታል።

የአጼዎቹ ስርዓት የኢትዮጵያን መሬትና የተፈጥሮ ሀብት ብቻ ሳይሆን ህዝብንም ጭምር እንደ ግል ንብረት ይቆጥር ስለነበር እንኳን ለዜጎች ዴሞክራሲያዊ መብት መከበር ይቅርና ለሰብዓዊ መብቶችም ቁብ የሚሰጥ ስርዓት አልነበሩም። የደርግ መንግስትም ቢሆን ሶሻሊሊስታዊ ስርዓትን አስፈናለሁ በሚል ሽፋን የለየለት ፋሽስትና አምባገነን መንግስት ነበር፡፡ ይህንን የተበላሸ ፖለቲካዊ ሁኔታ በሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ መልኩ ለመቀየርና አማራጭ ሃሳብ ለህዝብ ለማቅረብ ትግል የጀመሩትን ወጣት ምሁራን በግልጽና በአደባባይ ከመጨፍጨፉም በላይ ሁሉም ነገር ወደ ጦር ግንባር በሚል የጥፋት ፖሊሲው አገሪቱን ወደ ውድቀቷ ህዝቡን ወደከፋ ድህነት እንዲያመራ አድርጓታል። የደርግ መንግስት በተከተለው የተሳሳተ አካሄድ አገሪቱን ከገደል አፋፍ አቁሟት ነበር።

ግንቦት ሃያ በአገራችን ታሪክ የበርካታ መልካም ነገሮች መሰረት ናት። የዛሬ 27 ዓመት ማለትም ግንቦት 20 ቀን 1983 ዓ.ም ኢህአዴግ መራሹ ሀይል አዲስ አበባን በመቆጣጠር አምባገነኑን የደርግን አገዛዝ ሙሉ በሙሉ ከስልጣን ያስወገደበት ዕለት ናት። በዚህም ሳቢያ ለ17 ዓመታት ሲካሄድ የነበረው ለዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ የተከፈለው እልህ አስጨራሽ የዕርስ በርስ ጦርነት ያበቃበት ዕለት ናት - ግንቦት ሃያ። ደርግ በሃይል በትረ ስልጣኑን ሲለቅ በርካቶች የኢትዮጵያ እጣ ፈንታ እንደ ሶማሊያ፣ ዮጐዝላቪያና ላይበሪያ ትሆናለች በማለት ሲናገሩና ሲጽፉ ነበር፡፡ ይሁንና ኢትዮጵያ እንደተሟረተባት ሳይሆን በተቃራኒው ለመሆን ያበቃት በወቅቱ ኢህአዴግ የተከተለው ሁሉንም አካቶ መያዝ የሚያስችል የሽግግር መንግስት እንዲመሰረት በማድረጉ ነው። በድርግ ውድቀት ማግስት በአገራችን ከ17 በላይ የታጠቁ የብሄር፣ የፖለቲካ፣ የሃይማኖት ሃይሎች ድርሻ ድርሻቸውን ለመቀራመት ባሰፈሰፉበት ወቅት ኢህአዴግ የተከተለው በሳል አካሄድ አገሪቱን ከመበታተን ታድጓታል። ለዚህም ይመስለኛል በርካቶች ኢህአዴግ ።

ግንቦት 20 ቀን 1983 ዓ.ም ለኢትጵያና ለህዝቦቿ ከበርካታ ስቃይ እፎይታን ያስገኘች፣ ለዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ መሠረት የጣለችና ለብሔሮች፣ብሔረሰቦችና ህዝቦች የነፃነትና የዕኩልነት መብት መረጋገጥ ፋና ወጊ የሆነች ዕለት በመሆኗ በአገሪቱ የፖለቲካ ታሪክ ውስጥ ለአብዛኛዎቹ የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ዘንድ በመልካምነት ስትዘከር፣ በገዥነት ስልጣናቸው በህዝቦች ጫንቃ ላይ ተቀምጠው ለነበሩት የባለፉት ስርዓት አቀንቃኞች ደግሞ ገደቢስ ቀን ተደርጋ ትወሰዳለች። የህዝብ

ፍላጎትና ጥቅም ሁሌም ሊቀድም ይገባልና ጥቂቶች ግንቦት ሃያን በመልካም ባይመለከቷትም በብዙዎች የኢትዮጵያ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች ደምቃ የምትከበር ዕለት ለመሆን በቅታለች።

ከላይ ለማንሳት እንደሞከርኩት ግንቦት 20 ቀን 1983 ዓ.ም በኢትዮጵያ ታሪክ ጉልህ ስፍራ ካላቸው ቀናት መካከል በቀዳሚነት የምትነሳ ዕለት ናት። ግንቦት 20 የኢትዮጵያ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች ማንነታቸውን ያረጋገጡበት፣ ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶቻቸው በሃይል ያስከበሩበት፣ የኢትዮጵያ አንድነት በህዝቦች መፈቃቀድ፣ በዕኩልነትና በነጻነት በጽኑ መሰረት ላይ የመሰረቱባት ዕለት ናት። ከግንቦት 20 1983 ዓ ም ማግስት በርካታ ለውጦች በአገራችን ተመዝግበዋል። እንደእኔ የመጀመሪያው የደርግ መንግስት ሲከተለው የነበረውን የዕዝ ኢኮኖሚ ስርዓት ሙሉ በሙሉ በመቀየር በነጻ ገበያ ስርዓት የሚመራ የኢኮኖሚ ፖሊሲ እንዲተካ መደረጉ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ አገሪቱ ቀደም ሲል በዘውዳዊና ፍጹም አምባገነናዊ ብቻ ሳይሆን በጠንካራ አሀዳዊ ሥርዓት ስትመራ በመቆየቷ ከሽግግር ወቅት ጀምሮ ባልተማከለ፣ዴሞክራሲያዊና ፌዴራላዊ በሆነ የመንግስት አስተዳደር ሥርዓት እንድትመራ ሁኔታዎች መመቻቸታቸው ነው፡፡ የፌዴራል ስርዓቱ ኢትዮጵያን ከመበታተን አደጋ ታድጎ በፈጣን ኢኮኖሚ መዋቅር ውስጥ እንድትጓዝ አድርጓታል

በሽግግሩ ወቅት ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች በፌዴራል ስርዓት መተዳደር ያስገኘላቸውን ጥቅም በመረዳት ከ1987 ዓ.ም ጀምሮ ይኸው ያልተማከለው አስተዳደር ስርዓት ህገ-መንግስታዊ ዋስትና እንዲያገኝ አድርገዋል። በዚህም ምክንያት አብዛኛዎቹ የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ራሣቸውን በራሳቸው ማስተዳደር ከመቻላቸውም በላይ በጋራ ጉዳዮችም ላይ እኩል ተሳታፊ የሚሆኑበት የፌዴራል መንግስትም አዋቀሩ፡፡ ዛሬ ኢትዮጵያ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች ስለጭቆና ወይም ስለነጻነት መጓደል የሚያነሱት ምሬት የለም።

የመድብለ ፓርቲ ስርዓት የኢፌዴሪ ህገ-መንግስት አንዱ ውጤት ነው። በአገራችን የመድብለ ፓርቲ የፖለቲካ ሥርአትን በመከተሏ ህዝቦች ይበጀናል፣ ይወክለናል የእኔ ነው የሚሉትን ተወካያቸውን በየአምስት ዓመት በነጻነት መምርጥ ችለዋል። እስካሁን አምስት አገራዊና ክልላዊ ምርጫዎችን በነጻነት ተካሂደዋል። ህዝቦች የተጎናጸፉት የፈለጉትን የመምረጥ መብት ብቻ ሳይሆን ውክልናውን በአግባብ

አልተወጣም፣ አንፈልገውም ያሉትንም ተወካያቸውን በፈለጉበት ወቅት ማንሳት እንደሚችሉም በተግባር አረጋግጠዋል።

የኢፌዴሪ ህገ-መንግስት ሃሳብን በሰላማዊ መንገድ የመግለጽ መብትንም ለዜጎች አጎናጽፏል። ቅድመ ምርመራን ከማስቀረት ጀምሮ የፕሬስ ነጻነትን በግልጽ በማዋጁ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ የሚስማማውን የፖለቲካ አስተሳሰብ እንዲያራምድና የመሰለውንም ሀሳብ በነጻነት እንዲገልጽ ዕድል ተፈጥሮለታል። ባለፉት 27 ዓመታት አንዳንዶች ሃሳብን በነጻነት የመግለጽ መብትን ተጠቅመው አገርን ሊያፈርስ ህዝብን ሊያጫርስ የሚችል ተግባራትን ሲያከናውኑም ታይተዋል። እነዚህ ሃይሎች የህግ የበላይነትን አይቀበሉም፣ የብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች ዕኩልነት አያምኑም፣ እነዚህ ሃይሎች አንድነት የሚሉት የቀድሞ ስርዓቶች ያራምዱ የነበሩት የሃይል አንድነት እንጂ በህዝቦች መፈቃቀድ ላይ መሰረት ያደረገውን የአዲሲቷን ኢትዮጵያ አንድነት አይደለም። በመሆኑም በነጻ ፕሬስ ስም በጥፋት ብዕራቸው አገራችንን ሊበታትኗት፣ ህዝቡን ሊያጫርሱት እንደነበር የቅርብ ጊዜ ትውስታችን ነው። እንዲህ ያለን ቅጥ ያጣ አካሄድን ሃይ ማለት ፕሬስን መቃወም አይደለም። የህግ የበላይነት በየትኛውም ቦታና ጊዜ ማረጋገጥ የሁሉም አገር ወዳድ ዜጋ ግዴታ ነው። ፕሬስ ነጻ ይሁን ሲባል ልቅና ምንም ዓይነት ቁጥጥር አይደረግበትም ማለት አይደለም። ፕሬስ ልማትን የሚያፋጥን፣ ዴሞክራሲን የሚያጎለብተውን ያህል በተቃራኒው ከቆመም ጉዳቱ የከፋ ነው።

ባለፉት 27 ዓመታት በአገራችን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ረገድም ከፍተኛ ለውጥ ተመዝግቧል፡፡ ከሁሉም ነገር ወደ ጦር ግንባር ወደ ሁሉም ነገር ወደ ልማት የሚል የፖሊሲ ለውጥ በመደረጉ በተለይም ደግሞ ባለፉት 16/17 ዓመታት እጅግ ፈጣን የሆነ የኢኮኖሚ እድገት ማስመዝገብ ተችሏል፡፡ አገራችን አለምን ያስደመመ ፈጣንና ቀጣይነት ያለው የኢኮኖሚ የዕድገት ምህዋር ውስጥ መግባት ችላለች። አገራችን በመሰረተ ልማት ግንባታም እጅግ ስኬታማ መሆን ችላለች። የትምህርት ሽፋኑ በከፍተኛ ሁኔታ ማደግና የጤና አገልግሎቱ በፍጥነት መስፋፋትም ሌላኛው በግልጽ የሚታይና በእጅ የሚጨበጥ የኢኮኖሚ ዕድገቱ የወለደው ማህበራዊ ለውጥ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል፡፡ ከ1995 ዓ.ም በፊት የነበሩት ዓመታት በአገራችን የመንግስት ትኩረት ሰላምና መረጋጋትን በአስተማማኝ ሁኔታ ማስፈር ላይ የነበረ በመሆኑ እንዳሁኑ ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት የተመዘገበበት ወቅት አልነበረም።

ይሁንና አጠቃላይ የሀገሪቱ ኢኮኖሚ በአብዛኛው በአምስትና በስድስት ፐርሰንት እያደገ እንደነበር ማስታወሱ ተገቢ ነው።

የመልካም አስተዳዳር ችግሮች በየትኛውም ዓለም ያሉ ወደፊትም የሚኖሩ ነገሮች እንደሆኑ ታሳቢ ማድረግ ተገቢ ነው። መንግስት የመልካም አስተዳዳር ችግሮችን ለመቅረፍ የሚያስችሉ በርካታ ስራዎችን በማከናወን ላይ ይገኛል። ይሁንና የታሰበው ስኬት ሊመጣ አልቻለም። የመልካም አስተዳደር ችግሮች ሊቀረፉ የሚችሉት በመነጋገርና በመወያየት እንጂ በአመጽና ነውጥ ሊሆን አይችልም። በመሆኑም መንግስት በጥልቅ ተሃድሶው ሂደት በመልካም አስተዳደር እጦት የሚማረረውን የህብረተሰብ ክፍል ቅሬታ ለመፍታት የሚያደርገውን እንቅስቃሴ አሁንም ችላ ሊለው አይገባም። ይህ የመንግስት ጥረት ውጤታማ የሚሆነው በህዝብ ሲታጀብ በመሆኑ እያንዳንዱ ዜጋ ለመልካም አስተዳዳር መስፈን የበኩሉን ሊወጣ ይገባል።

ግንቦት ሃያ የኢትዮጵያ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች ዴሞክራሲያዊ ስርዓትንና መልካም አስተዳደርን ለማስፈን፣ የተረጋጋ የፖለቲካ ስርዓት ለመገንባት፣ ማህበራዊ ፍትህን ለማንገስ ዘላቂ ሰላምን ለማርጋገጥና ህዝቡ በየደረጃው ዕኩል ተጠቃሚ የሚሆንበት ፈጣን ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ለማስመዝገብ የሚያስችል መሰረት የሆነች ዕለት ናት። የአዲሲቷ ኢትዮጵያ የህልውና ዋስትና የሆነው የፌዴራል ስርዓታችን የ“ግንቦት ሃያ” ዋንኛ ፍሬ ነው። አንዳንዶች ሆን ብለው ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ የፌዴራል ስርዓቱን ለማብጠለጠል ሲሞክሩ ተመልክተናል። ይህ የፌዴራል ስርዓት ኢትዮጵያን ከመበታተን አደጋ ታድጎ በስኬት እንድትጓዝ ያደረገ ነው። ይህን የፌዴራል ስርዓት መነካካት፣ በትንሹም በትልቁም ማንሳትና መጣል አዲሲቷን ኢትዮጵያ በቅጡ አለመረዳት ይመስለኛል።